የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5 እና 6

1. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቁጥር 8 ላይ ጴጥሮስ ጌታችንን “እኔ ኀጢአተኛ ሰው ነኝና አቤቱ ከኔ ፈቀቅ በል” ያለው ለምን ነበር?
ሀ) በባሕር ያለውን መርምሮ ያወቀ ኃጢአቴን መርምሮ አውቆ እንደምን ይፈርድብኝ ይሆን ብሎ አስቦ
ለ) ምትሐተኛ መስሎት አንዳች ነገር እንዳያደርገው ስለፈራ
ሐ) የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ተገልጦለት
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

2. በምዕራፍ 5 መጀመሪያ ላይ የሚገኙት ሁለት መርከቦች ምሳሌነታቸው ለምንድን ነው?
ሀ) ጌታ የተቀመጠባት መርከብ የጽድቅ ምሳሌ ያልተቀመጠባት የኃጢአት ምሳሌ
ለ) ጌታ የተቀመጠባት መርከብ የወንጌል ምሳሌ ያልተቀመጠባት የኦሪት ምሳሌ
ሐ) በምንም አይመሰሉም
መ) ሀ እና ለ

3. "ዛሬን የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው" ሲል ምን አይነት ኃዘንን ለማለት ነው?
ሀ) እናት አባት ሞተብኝ፣ ዘመድ ርስት ሄደብኝ ብሎ ማዘን
ለ) የራስን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን
ሐ) የባልንጀራን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን
መ) የሰማዕታትን መከራ፣ የክርስቶስን ሞት እያሰቡ ማዘን
ሠ) ሁሉም
ረ) ከ"ሀ" በስተቀር ሁሉም

4. ጌታ 12ቱን ሐዋርያትን ከመምረጡ በፊት...
ሀ) ያስተምር ነበር
ለ) ተአምራትን ያደርግ ነበር
ሐ) ወደ ተራራ ወጥቶ ይጸልይ ነበር
መ) ሁሉም

5. ከ12ቱ ሐዋርያት ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) በርተሎሜዎስ ለ) ፊልጶስ ሐ) ናትናኤል መ) በርናባስ

6. "የአሮጌ ረዋት አዲስ የወይን ጠጅ አይጨምሩም፤ ቢጨመር ግን ረዋቱ ይቀደዳል፤ ወይኑም ይፈሳል፤ ረዋቱም ይበላሻል፤ ነገር ግን አዲሱን ወይን በ አዲስ ረዋት ይሾሙታል፤ ሁለቱም እርስ በርሳቸው ይጠባበቃሉ።" የሚለው ቃል የሚያመለክተው...
ሀ) ሐዋርያት በልጅነት ባልታደሰ ሰውነታቸው ሕጉን(ጾምን) ጠብቁ እንደማይባሉ
ለ) ሐዋርያት ወይን ከጠጡ በሓላ መጾም እንደሚችሉ
ሐ) ሐዋርያት ሰውነታቸው በልጅነት ሲታደስ ሕጉን(ወንጌልን፣ ጾምን) እንደሚጠብቁ እርሱም እንደሚጠብቃቸው
መ) ሀ እና ሐ

7. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ጌታ ለምጻሙን ሰው እንዴት አዳነው?
ሀ) ምራቁን ከመሬት እንትፍ ብሎ ዳሰሰው
ለ) እጁን ዘርግቶ ዳሰሰው
ሐ) "እወዳለሁ ንጻ" አለው
መ) ለ እና ሐ

8. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ጌታ ለምጻሙን ሰው ካዳነው በኋላ...
ሀ) ለማንም እንዳይናገር ከለከለው
ለ) ራሱን ለካህን እንዲያስመረምር አዘዘው
ሐ) ሙሴ እንዳዘዘ መባህን አቅርብ አለው
መ) ሁሉም

9. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ ጌታ በተራራ ላይ ከአስተማረው ውጭ የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ለሚበድሏችሁ 77 እጥፍ መልሱ
ለ) ለሚጠሏችሁ መልካም አድርጉ
ሐ) ስለ ሰው ልጅ ክፉ ስም ቢአወጡላችሁ ብፁዓን ናችሁ
መ) ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ

10."መሠረቱን አጥልቆ ቁፍሮ የመሠረተና ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ" የተባለው...
ሀ) ቃሉን ሰምቶ የሚያደርግ
ለ) 'ጎርፍ' በመጣ ጊዜ በታላቅ አወዳደቅ የሚወድቅ
ሐ) ቃሉን ሰምቶ የማይፈጽም
መ) ለ እና ሐ

11. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5 በቤቱ ታላቅ ግብዣ ያደረገው ቀራጭ ማን ነው?
ሀ) ማቴዎስ ለ) ሌዊ ሐ) በደንብ ያልታወቀ ሌላ ነጋዴ መ) ሀ እና ለ

12.የዘብዴዎስ ልጆች ተብለው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት ማን እና ማን ናቸው?
ሀ) ስምዖን እና እንድርያስ
ለ)ያዕቆብ እና ዮሐንስ
ሐ)ቶማስ እና በርተሎሜዎስ
መ)ፊልጶስ እና ናትናኤል

13. ጌታችን "አትፍራ ከእንግዲህ ወዲህስ ሰውን ታጠምዳለህ" ያለው ማንን ነው?
ሀ)ስምዖን ጴጥሮስ
ለ)ስምዖን ቀናኢ
ሐ)ዮሐንስ
መ)ይሁዳ

14.የሰንበት ጌታ ማን ነው?
ሀ)መላእክት
ለ)እንስሳት
ሐ)የሰው ልጅ
መ)ሁሉም

15."አልጋህን ተሸክመህ ሂድ " ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያዳነው ምንን ተመልክቶ ነው?
ሀ)በዙሪያው የነበሩት ሰዎች ተአምር ማየት መፈለጋቸውን ተረድቶ
ለ)በአልጋ ላይ ያለው ሰው ለምኖት
ሐ) በአልጋ ላይ ያለው ተስፋ መቁረጡን ተመልክቶ
መ)በጣራ ላይ ያስገቡትን ሰዎች እምነት ተመልክቶ

16.እጁ የሰለለችውን ሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየት እና መች አዳነው?
ሀ)በሰንበት እና በቤተመቅደስ
ለ)በሰንበት እና በምኩራብ
ሐ)በሰንበት ማግስት እና በቤተመቅደስ
መ)በሰንበት ማግስት እና በምኩራብ

17.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ መልካም ፍሬ ያለው መልካም ዛፍ ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ)ወይን
ለ)ደንደር
ሐ)እሾህ
መ)ለ እና ሐ

18.ጻፎችና ፈሪሳውያን ይሳደባል ያሉት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለምንድን ነው?
ሀ)እግዚአብሔር መሆኑን ስላላወቁ ኃጢአትን ለማስተሥረይ ስልጣን የለውም ብለው
ለ)ለምን ተአምራትን ይፈፅማል ብለው
ሐ)ሲያድን አይተው ደስ ብሏቸው
መ)ሁሉም

19.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መፃጉዕን አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ለምን አለው?
ሀ) ሙሉ ለሙሉ መዳኑን ለማሳየት
ለ) ሁልጊዜ የተሸከመችውን አልጋ ውለታ እንዳይረሳ
ሐ) ላዳነበት ክፍያ እንደማይፈልግ ለመንገር ንብረቱን ይዞት እንዲሄድ ነገረው
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

20. በምዕራፍ 6 ላይ ጌታችን በተራራ ላይ ያስተማረው ትምህርት ምን በመባል ይታወቃል?
ሀ) አንቀጸ ብፁዓን ለ) አንቀጸ ሰንበት ሐ) አንቀጸ ሐዋርያት መ) ሁሉም መልስ ናቸው